ስለ ሪሰርች አፕቴክ ምንነትና የኤፍ.ኤስ.ኤስ. (FSS) ተሞክሮ

በአበራ ወልደኪዳን አሸብር

1. መግቢያ

ጥናትና ምርምር ሳይንሳዊ ዘዴን መሠረት አድርጎ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ወይም በተለያዩ መስኮች አዳዲስ ንድፈ ሀሳቦችን ወይም ዕውቀት ለማፍለቅ ወይም የአንድን ፕሮግራም፣ፖሊሲ፣ የአሰራር ዘዴና ሌሎች ነገሮች በተጠቃሚዎች ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት ለማወቅ በሰዎችወይም በሌሎች ማናቸውም ነገሮች ላይ የሚካሄድ የምርምር ዘርፍ ነው።

የጥናትና ምርምር እድገት የተለያዩ ደረጃዎችን ያለፈ ቢሆንም አሁን ባለንበት ዘመን በሁለንተናዊ መልኩ እያደገ እና እጅግ እየተራቀቀ በመምጣቱ እንደ ዋና ችግር መፍቻ፣ በነበረው እውቀት ላይ ሌላ እውቀት መጨመሪያ እና የወደፊቷን አለም በተሻለ መንገድ መመልከቻ መንገድ እየሆነ እንደመጣ ይታመናል። ወደ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ስንመጣ በዓለማችን በዚህ የጥናት ዘርፍ የተሰማሩ በርካታ የፖሊሲ ጥናት ተቋማት እንዳሉ የሚታወቅ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት የሚገኙ የምርምር ተቋማት በፖሊሲ ላይ አተኩረው የሚሠሩት የሚያወጧቸውን ሥራዎች ለመንግሥት ውሳኔ አሰጣጥ እንደ ግብዓት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ነው። በእነዚህ አገሮች ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመሥርተው የተሠሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በተለይ የፖሊሲ ጥናት ተቋማት፣ በመንግሥትና በሕዝቡ መካከል መደበኛ ያልሆነ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ።

በመሆኑም የፖሊሲ ጥናት ተቋማት በተመራማሪዎች፣ በሕዝቡና በውሳኔ ሰጪዎች መካከል የሃሳብ ልውውጥ ባህል እንዲዳብር ይሠራሉ። እነዚህ ተቋማት በአብዛኛው በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖሊሲዎች ላይ አተኩረው በቋሚነት ጥናት ያደርጋሉ። የጥናት ውጤቶቻቸው ለሕዝቡና ለፖሊሲ አውጭዎች እንዲደርሱም ያደርጋሉ። ጥልቅ የሆን ጥናትና ምርምር በማካሄድ በሥራ ላይ ያሉት ፖሊሲዎች እንዴት እየሠሩ እንደሆነና፣ እስካሁን የተገኘው ውጤትና በትግበራው ሂደት የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ ለመንግሥትና ለባለድርሻ አካላት ያቀርባሉ። ይህ ደግሞ ፖሊሲ አውጪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሕዝቡም በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጥ ያስችላል። መሰል ተቋማት በኢትዮጵያም የሚገኝ ሲሆን ከነዚህም ተቋማት መካከል ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ ኤስ.ኤስ ) የተባለው አንጋፋ የፖሊሲ ጥናትና በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። ተቋሙ በአገሪቱ የመጀመሪያው ገለልተኛ የፖሊሲ ጥናት ተቋም ነው።

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ.ኤስ.ኤስ.) በማሕበራዊና ልማታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድና፤ ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት እንዲያደርጉ መድረኮችን የሚያዘጋጅ፤ መንግስታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ሀገር-በቀል የሲቪክ ማሕበረሰብ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ባለፉት 25 ዓመታት በበርካታ የፖሊሲ ጉዳዮች ዙርያ ፖሊሲ ተኮር ምርምርና የህዝባዊ ውይይት መድረኮችን ያካሄደ ሲሆን ውጤቶቻቸውን በተለያዩ ህትመቶችና የጋዜጣ አምዶችን ጨምሮ በሳምንታዊ የራድዮ ፕሮግራሞች፣ በቴሌቪዥን እንዲሁም በድረ-ገፅና ማህበራዊ ትስስር ገፆቹ አማካኝነት ለተለያዩ የባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ አድርጎ አመርቂ ውጤት ለማስመዝገብ ችሏል። ድርጅቱ ከምርምርና የውይይት መድረኮች የሚፈልቁ የፖሊሲ ምክረሃሳቦችን በተለያዩ የህትመትና የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለመንግሥትና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሁኑ በማድረግ፣ የሚፈለገው የፖሊሲ ለውጥ እንዲመጣ የማድረግ ሥራዎችን ይሠራል። በተግባር ተፈትነው ስኬታማ የጥናትና ምርምር አውሳሰድ ስልቶችና አዳዲስ አቀራረብን ሲተገብር ቆይቷል።

በዚህ ፅሁፍ፣ የምርምር ግብአቶች በመንግሥትና ባለድርሻ አካላት ዘንድ ተአማኒነትና ተቀባይነት እንዲያገኙና ተግባራዊ ለውጥ እንዲመጣ ለማድርግ ከሚደረጉ ጥረቶች መካከል ሊጥቀስ የሚችልና በቅርቡ የአፍሪካ ከተሞች ጥናትና ምርምር ኮንሶርቲየም (ACRC) ጋር በመተባበር የተገበረዉን የተሻለ የምርምር አወሳሰድና ሥራ ላይ የማዋል ስልት city research uptake የተሰኘ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት የተወሰድውን ተሞክሮ ለማካፈልና መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይሞክራል።

2. ሪሰርች አፕቴክ ምንድነው?

እንደ ዓለም አቀፉ የልማት ቢሮ ትርጓሜ Research uptake (ሪሰርች አፕቴክ) የመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች፣ ፈፃሚዎች እና ሌሎች የልማት ተዋናዮች የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በተገቢው መንገድ ተቀብለው ጥቅም ላይ በማዋል ተግባራዊ ለውጥ ማምጣት የሚችሉበትን ሂደት የሚያሳልጥ አይነተኛ ስልት ነው። የሪሰርች አፕቴክ ሂደት በበርካታ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ተመራማሪዎችና ምሁራን በተለይም በፖሊሲ ጥናት ተቋማት ከሚካሄደው የተለመደው የጥናት አካሄድ በምን ይለያል? ይህን ጥያቄ ለመመለስ በእነዚህ ተቋማት የተለመደው የጥናትና ምርምር አካሄድ በአብዛኛው ምን ይመስላል የሚለዉን ማየት ጠቃሚ ይሆናል። በእነዚህ ተቋማትና ተመራማሪዎች በተለምዶ የሚካሄዱት ጥናቶች፣ ጥናቱ ከሚያተኩርባቸው ርዕሶች ብንጀምር በአብዛኛው በለጋሽ ድርጅቶች ፍላጎት ላይ የተመሠረተና በጥናቱ የመጨረሻ መዕራፍ ላይ የባለድርሻ አካላትን ይሁንታ ወይንም ማረጋገጫ ለማግኘት (validation) ሲባል ከሚዘጋጀው መድረክ ባለፈ፣ የጥናቱ ጉዳይ የሚመለከታቸው ፖሊሲ

አውጪዎችና ባለድርሻ አካላትን በጥናቱ ሂደት መጀመርያ ጀምሮ የማያሳትፍና የጥናት ውጤቱ አጠቃቀም ላይም የማያተኩር ነው።

በአንፃሩ ሪሰርች አፕቴክ ከዚህ የተለየ ነው። የፖሊሲ አውጪዎች፣ የጥናት ውጤቱን በአግባብነት የሚጠቀሙ አስፈፃሚዎች እና ሌሎች ተዋናዮች እንዲሁም ተመራማሪዎች ከጥናቱ ጥንስስ ጀምሮ በጥናት ሂደቱ በቀጥታ የሚሳተፉበት የአጠናን ሄደት ብቻ ሳይሆን የጥናት ውጤቶች ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ሁለንተናዊ የትናትና ምርምር ሂደት ነው። በአንድ የፖሊሲ ጉዳይ ዙሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን ( ትርጓሚዎችን ተጠቃሚዎችን ያገባኛል የሚሉ

ተቋማትና ተመራማሪዎችን በጥናቱ ሂደት የሚያሳትፍ የጥናት ዘዴ በመሆኑ የሚፈለገው የፖሊሲ ለውጥና የሁኔታዎች መሻሻል/መቀረፍ የሚያግዝ ውጤታማ መንገድ ነው። ስለሆነም በዚህ መልክ የተከወኑ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎች መሬት ላይ ያሉ ችግሮችን ለይቶ ለማውጣት የሚስችሉ መሆናቸው ሪሰርች አፕቴክ ከተለመደው የጥናትና

ምርምር ፕሮጀክቶች ትግበራ ልዩ ያደርገዋል። ይህ አካሄድ የመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች እና ፈፃሚዎች እንዲሁም የልማት ተዋናዮች በቀጥታ ተሳታፊ በሆኑበት የጥናት ሂድት የመነጨውን መረጃ ወይም እውቀት ተጠቅመው ተግባራዊ የማድረግ እድሉን በማስፋት ረገድ የሚኖረው

አስተዋፃኦ ትልቅ እንደሚሆን እሙን ነው። በአጠቃላይ፣ ሪሰርች አፕቴክ (research uptake) የጥናት ውጤቱ በፖሊሲ አውጪዎች፣ ተርጓሚዎች እና ሌሎች የልማት ሂደት ባለድርሻ አካላት በመረጃ የተደገፈ እውቀት አጥቃቀምን በማሳለጥ ረገድ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ማናቸዉንም አይነት ተግባርና እንቅስቃሴን ያጠቃልላል:: ተግባራቱ የሚከተሉትን ለመፈፀም ያለሙ ናቸው፡ የጥናቱ የወደፊት ተጠቃሚዎች ጋር በሚካሄዱ የውይይትን ምክክር መድረኮች አማካኝነት ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች/የጥናት መጠይቆች አግባብነት ያላቸው እንዲሆኑ ማረጋገጥ የጥናት ውጤቶቹን በአቻ ተመራማሪዎች በሚገመገሙ አካዳሚክ ጆርናሎች ማሰራጭት ብቻ የተወሰን ሳይሆን በውጤት ተኮር የስርጭት መንገድ የበለጠ ተደራሽነትን ማረጋገጥ በጥናቱ የተገኘውን በመረጃ የተመሰረተ ግኝት ለተለያዩ የባለድርሻ አካላትና ተደራሾች በሚመችና ጥቅም ላይ መዋል በሚችል መልኩ አንኳሩን ጭብጡን በማውጣት ማዘጋጀት (repackaging) የባለድርሻ አካላትን የጥናት መረጃን የማግኘት፤ የመገምገም፣ የመጠቀምና የመጭመቅ አቅምን መገንባት የጥናት ውጠቶችንና መረጃዎችን መጠቀም ዘዴ (Research uptake Approach ) አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከተቻለ ሁሉንም አልያም ከሁለት በላይ የሆኑትን መንገዶች ተግባር ላይ ማዋል የስኬት እድሉን ያሰፋዋል።

2.1. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ.( Stake holder Engagement)

የጥናት ስርፀት ፕሮጀክት (Research uptake ) የመጀመሪያ ደረጃ አግባብነት ያላቸው ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ለመለየት ያለመ የዳሰሳ ጥናት (Stake holder mapping) መሠራት ያኖርበታል፡፡ይህ ከሆነ በኋላ የእያንዳንዱን ባለድርሻ አካላት ፍላጎትና የጥናት ውጠቶችንና መረጃዎችን መጠቀም ዘዴ ለማገዝ የሚያስችል የተሳታፊነት ደረጃ መተንተን አስፈላጊ ይሆናል ።ከዚህ በመቀጠል የጥናት ዘዴውን ከባለድርሻ አካላት ጋር የማጣጣዳመር ሥራ ይሰራል ማለት ነው። ይህንኑ ተከትሎ ተከታታይነት ያለው የጋራ ተሳታፊነቱን የሚያመቻቹ መድረኮችን ማዘጋጀት ይጠይቃል።

2.2. የአቅም ግንባታ ( Capacity Building)

በዚህ የሁለተኛው የፕሮጀክት ትግበራ ሂደት ደረጃ፣ የጥናት ውጠቶችንና መረጃዎችን መጠቀም ዘዴ የጥናት ቡድኑ የውስጣዊና ውጫዊ አቅም ዳሰሳ ስራ የሚያካሂድበት ሲሆን በእውቀት፤ ክህሎት ፈጠራዎች እና አመለካከቶች አቅምን የሚያጎለብትበት ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ተከትሎ በመጨረሻ ክፍተቶች ካሉ የሚያሻሽልበትና ቡድኑ የአቅም ግንባታ እቅዶችንና ስልቶችን የሚዘጋጅበት ክፍል ነው። በዚህ የአተገባበር ደረጃ ሂደት የሚከተሉት ወሳኝ ክህሎቶች ላይ ያተኮኩራል። የመረጃ እውቀት (ሳይንሳዊ ጥናቶችን የመፈለግና ማግኘት እንዲሁም የመመዘን ክህሎት የጥናት ዘዴዎችን የመምረጥና የመተንተን ብቃት

የጥናት ውጤቶችን የማሰራጨት/ተግባቦትን ያጠቃልላል።

2.3. የምርምር ውጤቶች ስርጭት (communication)

የሚካሄደው ምርምር በጉዳዩ ላይ ባለው እውቀት ላይ የሚጨምር መሆን አለበት። በመሆኑም የጥናቱ ግኝት ሲቀርብ ከአሁን በፊት ካለው መረጃ ጋር በተነፃፃሪነት (context)። ሰለሆነም የሪሰርች አፕቴክ ፕሮጀክቱ የጥናት ቡድን ጥናቱን ከመጀመሩ በፊት ጥናቱ በሚያተኩርበት ርዕስ ዙርያ በቂ መረዳት ሊኖራቸው ይገባል። ስለሆነም የተዛማጅ ፅሁፍ ምልከታ(Litrature Review) እንዲያካሂዱ ይመከራል፡- የተዛማጅ

ፅሁፍ ምልከታ በሚጠናው ጥናት ዙሪያ ከዚህ በፊት በተጠኑ ጥናቶችን በጥልቀት ማየት ከማስቻሉም በላይ ምላሽ ያላገኙ ውይነም በበቂ ሁኔታ

ያልተዳሰሱ የባለድርሻ አካላትን ጥያቄዎች ማየትና ማካተት ያስችላል። ጥናቱ በዚህ መንገድ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ ግኝቶቹን በተለያዩ ኮንፈረንሶችና መድረኮች ለመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎችና ባለድርሻ አካላት ማቅረብ ይቻላል። የታዩ ክፍተቶችና ምክረሃሳቦች በቀላሉ ለማስረዳት መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል።

2.4. ክትትልና ግምገማ ( Monitring and Evaluation Up take)

ይህ የሪሰርች ፕሮጀክት ትግበራ ክፍል፣ የጥናቱን ሂደት የምንከታተልበትና በመጨርሻም የውጤቶቹን ጥራት የሚለካበት ክፍል ሲሆን ይህን ለመፈፀም የሚያስችልና ለዚህ ተግባር ታሰቦ የተዘጋጀ የመለኪያ መስፈርቶችን ማዘጋጀት የሚጠይቅ ነው እዚህ ላይ ዋናው ቁምነገር በዚህ መንገድ የሚካሄዱ ጥናቶች ከፍተኛ ጥራት ያላቸውና አግባብነት ወይንም ከነባራዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ የማረጋገጥ አስፈላጊነት ማስታወስ አስፈላጊ መሆኑን ነው። ከዚህ ግንዛቤ ውጪ የሚካሄዱ የሪሰርች አፕቴክ ጥናቶች ትርጉም የለሽ ይሆናሉ በቻ ሳይሆን በተለያየ መንገድ ጉዳት የሚያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ የተጠኑትን ጥናቶች ተደራሽ ማድረግንና ከባለደርሻ አካላት ጋር በመረጃ ላይ የተደገፍ የውይይት መድረኮችን ማካሄድን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ባለድርሻ አካላት የጥናት ዉጤቶችን በአግባቡ የመጠቀም ክህሎትን የማያጎለብት የአቅም ግንባታ መርሃ ግበችም በዚህ የተካተቱ ናቸው።

በአጠቃላይ፤ የጥናቱ ውጤትን ለመለካት የሚከተሉትን መስፈርቶች መጠቀም ይመከራል

1. ጥራት፣ ማረጋገጥ፣

2. ባለድርሻ አካላት በጥናት ውጤቶች ዙርያ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ማሳተፍና ተደራሽ ማድረግን፣

3. ጥናት ለማከናወንና ውጤቶችን የመረዳት፣ የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብር ማዘጋጀት

4. የFSS-ACRC Research Uptake ፕሮጀክት ትግበራ ሂደት ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ.ኤስ.ኤስ›) ከላይ በተገለፀው የረሰርች አፕቴክ ፕሮጀክት ተግባራዊ አ መመሪያ መሠረት የአፍሪካ ከተሞች ጥናት ጥምረት (Africa Cities Research Consortium) ከተባለ መረብ ጋር በመተባበር ለድርጅቱ የመጀመርያ የሆኑውን ፕሮጀክት ተግብሯል። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ACRC በአፍሪካ በለውጥ ላይ

የሚገኙትን የአፍሪካ ከተሞች ውስብስብ ተግዳሮቶችና ፈተናዎችን ለመፍታት ላይ ያለመ፣ የተቀናጀ የጥናትና ምርምር መርሃ-ግብሮችን የሚያካሂድ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ግቡ ያደረገው የተወሳሰበውን የከተማ እድገት ችግሮችን እና ተግዳሮቶችን በመመርመርና በማጥናት በማደግ ያሉ የአፍሪካ ሃገራትን ችግር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ፣ የነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታና የከተሞች አገልግሎትን ለማሻሳል ይሠራል።

በ‹‹ዩናይትድ ኪንግደም›› (Foreign Common Wealth and Development Office -FCDO)

በሚያደረገው የገንዘብ ድጋፍ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በ12 የአፍሪካ ከተማዎች የሚካሄደው የጥናት መርሃ ግብር ዋና አላማ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥናቶችን በማድረግ ዕውቀትና መረጃን በማፍለቅ የከተማ ነዎሪዎችን በተለይም የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም አገልግሎቶች እና ዕድሎች እንዲሻሻሉ ማድረግ ነው። ይህ ፕሮጀክት በሃገሪቱ የሚገኘውን የምርምር ስርዓት በማዳበር በጠንካራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ ተመስርቶ አዳዲስ አመለካከቶችን እና አካሄዶችን በማፍለቅ የከተማ ልማት ተሀድሶ ጥረቶችን የማገዝ ሥራ ይሰራል። በዚህ የጥናት ዘዴና አቅጣጫ መሠረት በሶስት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተንተርሶ የአፍሪካ ፤የዕድገት ማነቆዎችን በመረዳት ፤ፖሊሲዎችንና ፤የድርጊት መርሃ ግብሮችን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያስችል ማድረግ ነው።

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS ) ከአፍሪካ ከተሞች ጥናት ጥምረት (Africa Cities Research Consortium (ACEEC) ጋር በመሆን በቅርቡ የጠናቀቀው የከተማ ጥናት በሶስት ጉዳዮች ማለትም፡ የመኖርያ ቤቶች ጉዳይ (Housing), መዋቅራዊ ለውጥ (Structural Transformation) እና የወጣቶች አቅም እና ክህሎት (Youth Capabilities) በሚሉ ዓበይት ርእሶች ዙርያ ያተኩሩ ነበሩ። በዚህም መሠረት ደርጅቱ ከላይ በተገለፀው የሪሰርች አሠራር ተግባራዊ መመርያን ከሞላ ጎደል በመከተል ስኬታማ ሊባል የሚችል የሪሰርች አፕቴክ ፕሮጀክት የተገበረ ሲሆን መረጃ ለመስጠት ያህል በዚህ መንገድ ለአንድ ዓመት በላይ የተከናወኑትን ተግባራት በዚህ አጭር ፅሁፍ የማይቻል በመሆኑ፣ ጠቅሌል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡ በፕሮጀክት እቅድና ትግበራ ዝግጅት ወቅት የፕሮጀክት ሃሳቦች ከተሰበሰቡ

በኃላ ወደ ፕሮጀክት ዝግጅት ተግባር የሚያልፉና ብቁ የሆኑ ሃሳቦችን ለመምረጥ በመጀመሪያ የድርጅቱን ሁኔታ፤ የድርጅቱን ሃብት እና የሰው ሃይል ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለውን የመምረጥ ተግባር ተከናውኗል። በመጀመርያ ደረጃ በሚካሄድ ዳሰሳ ባለድርሻ አካላቱ ተለይተው ከወጡ በሁዋላ በሚዘጋጅ መድረክ ጥናቱ ሊያተኩር በታሰበው የፖሊሲ ጉዳይ ዙርያ ከእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ሃሳብ ከመሰብሰብ ጀምሮ ባለድርሻ አካላቱ በሚካሄዱ ተከታታይ መድረኮች በጥናቱ አካሄድ፣ መረጃ በመስጠት፣ በትንተና እና በሌሎች እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉበት እንዲሁኑ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

በፕሮጄክቱ መጀመርያ የከተማው መስተዳድር ባለሥልጣናትን ጨምሮ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሁኑ ድርጅቶች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ የጥናት ቡድኑ ባቀርበው ጥናታዊ ፅሁፎች መነሻነት ንሰፊ ውይይት ተካሂዷል።ለውይይት ሰፋ ያለ የውይይት ጊዜ ተሰጥቶት ባለደሻ አካላት በጥናቱ ሊካተቱ የሚገባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ለመሰብሰብ ተችሏል። መድረኩ ተሳታፊዎች ቀጣይነት ያለው ተሳታፊነት አስፈላጊነት ላይ በማመን ቃል የገቡበት በመሆኑ የሚቀጥለውን የፕሮጀክት ሂደት ለማሳለጥ ምቹ መደላድል የፈጠረ ነበር።

በፕሮጀክቱ ትግበራ ሂደት የተጠቃሚዎች ተሳትፎና ግንኙነት ክትትል/stakeholder participation & contact Monitoring/ የተጠቃሚው ክፍል ተሳትፎ ደረጃ የሚጠበቀውን ያክል መሆኑን ለማረጋገጥና የተሻለ ተሳትፎ እንዲኖር እርምጃ ለመውሰድ የሚረዳ ክትትል ተደርጓል። በመቀጠልም የጥናት ቡድኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ደርጅቶች ባላሞያዎች ጋር አነስተኛ የምክክርና ሃሳብ የመሰብሰብ ሥራዎች ተሰርተዋል።

ከዚህ በመቀጠል የአፍሪካ ከተሞች ጥናት ጥምረት (Africa Cities Research Consortium የጥናት ቡድኖች የአዲስ አበባ ከተማ ፅ/ቤት ባለሥልጣናት በከተማዋ መስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተውጣጡ ባለሙያወች ጋር በጥናቱ አካሄድና በትብብር ስለሚሰራባቸው የስራ መስኮች ሃሳብ ተለዋውጧል። ጠቃሚ ሃሳቦችም ለመሰብሰብ ተችሏል። የምርምርና ስርፀት ፕሮጄክቱ፣ ከከተማዋ የልማት ግቦች ጋር የማጣመር አስፈላጊነትና በእውቀትና ልምድ ልውውጥ ዙሪያ ጠቃሚ ውይይት ተደርጓል። የፕሮጀክቱ ውጤታማነትና ተፅዕኖን ለመለካት የሚያስችል መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሂደት ተካሂዷል።

በተጨማሪ የጥናት ቡድኑ በተለያዩ የውይይትና የምክክር መደረኮች በፕሮጄክቱ ሦስት ዋና ርዕሶች ዙርያ በመካሄድ ላይ ባሉ የጥናት ሂደቶች እና በውጥን ደረጃ ያሉ የጥናት ክንውኖች ላይ ሰፊ ገለፃ አቅርበዋል። ከዚህ ፕሮጄክት ትግበራ ጎን ለጎን ፎረም ፎር ሶሻል ሳይንስ ከኢትዮጵያ የከትሞች ማህበራት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል። የኢትዮጵያ ከተሞች ማህበር በከተሞች መካከል የልምድና እውቀት ልውውጥ የሚያሳልጥ የጋራ መድረክ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ማህበሩ ከ ፎረም ፎር ሶሻል ሳይንስ/ የአፍሪካ ከተሞች ጥናት ጥምረት የፖሊሲ ጥናት ጋር የፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ጠቃሚነቱ የጎላ መሆኑን አስምረውበታል። የመግባቢያ ሰነዱ የሁለቱ ድርጅቶች በጋራ ለመስራት የሚችሉበትን መንገዶች ለመዳሰስ ለወደፊት የሚተገበሩ የጥናት ሀሳቦች ፤ የጥናት ውጠቶችንና መረጃዎችን መጠቀም (Research uptake) ላይ በጋራ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ያስችላቸዋል።

በ የሪሰርች አፕቴክ ቡድን የተግባቦትና የጥናቱ ውጤቶች ተደራሽ የሚያደርግበት ግልፅ የሆነ የግንኙነትና የተግባቦት መረብ አሰራር እንደሚከተል ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ሁለም በመድረኩ የተገኙ ኣካላት በጥናቱ ሂደት ላይ በጋራ የመስራት አስፈላጊነት ላይ በመስማማት ውይይታቸውን አጠናቀዋል። የጥናት ቡድኖቹ የትናት ግንታቸዉንና በእያንዳንዱ አብይ ጉዳይ ያላቸውን በመረጃ የተደገፈ ምክረሃሳቦች ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተገኙበተና ብጥልቅ በሳተፉበት የአንድ ቀን የፕሮጄክት ማጠቃለያ መርሃ ግብር አቅርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዶ በቀጣይ የስራ ግንኙንቶችና አቅጣጫዎች ላይ ስምምነት ተድርሷል። በመጨረሻም ፕሮጄክቱ በይፋ ተጠናቋል። እንደሚታወቀው አንድ የጥናት ሥራ እንደሁኔታው ስፋትና ጥልቀት አለው። ስለሆነም ጥናቱን ከመጀመሪያው

እስከ መጨረሻው አንብቦ ለመረዳት ጊዜ የሚጠይቅ ጉዳይ ይሆናል። የጥናቱን ፍሬ ነገር በቀላሉ እንዲረዱት አሳጥሮ ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ አበይት የሆኑትን ግኝቶች ባጭሩ በማዘጋጀት ግኝቶችንም በተለያዩ መንገዶች ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ተደርገዋል።

5. በፕሮጄክቱ ከተገኙ ቁልፍ የጥናቱ ውጤቶች መካከል በውጣቶች ክህሎት የጥናት ቡደን፡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ወጣቶች በከፋ የጉልበት ብዝበዛና በቂ ባልሆነ የጤና አግልግሎትና ሽፋን ሚያጋጥማቸው መሆኑን በአጠቃላይ ጠቃሚነት ያለው ተቋዋማዊና የፖሊሴ ማዕቀፍ ከየስራ ባህሪያቸው ጋር ተያይዞ እነደሚያስፈልጋቸው ፡ በከተማው ያሉ ኢነተርፕራይዞች የተወሰነ የእደገት እና ጥራቱን የጠበቀ

ግብአቶችን ለማግኘት እየታገሉ መሆኑን ፤ የመብቶች ተደራሽነትን ለማሳለጥ የተዘጋጁ አቅጣጫዎችንና እንቅስቃሴዎች በተለያዩና በተዛመዱ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የግልና የመንግሰት የጋራ ባለቤት መዴሎች እየተሸጋገሩ መሀኑን ያሳያሉ። የከተማ አገልግሎት አሠራሮች፡ የ 3.8 ሚሊዮን ነዋሪዎች የሆነችው አዲስ አበባ መጠን ሰፊ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ችግሮችና የከተማና የማህበራዊ አገልግሎቶች ጥያቄዎች እየተበራከቱባት ትገኛለች፡፡በቂ ያልነው የከተማ አገልግሎት አሰጣጥ ፤

በውሃ፤የንጽህናና የኃይል የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ፤ የጤናእንክብካቤ የምግብ ስርጭት፤ የፋይናንስና የህግና ሥርዓት አፈጻጸም ችግሮች ውስጥ ትገኛለች። እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮችንና ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ፎረም ፎር ሶሻል ሳይንስ/ የአፍሪካ ከተሞች ጥናት ጥምረት ከኢትዮጵያ የቤት ማህበራት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መፈራሙ የምርምር ስርዓት በማዳበር በጠንካራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ ተመስርቶ አዳዲስ አመለካከቶችን እና አካሄዶችን በማፍለቅ የከተማ ልማት ተሀድሶ ጥረቶችን ለማገዝ የከተማችንን የዕድገት ማነቆዎችን በመረዳት እና ለመገንዘብ ፤ፖሊሲዎችን ፤ የድርጊት መርሃ ግብሮችን በተሸለ ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል።

በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚሠሩ ሴት ሠራተኞች የሚደርስባቸው ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች፡ በአኢንዱስትሪ ፓርኮች የተፈጠረው የሥራ ዕድል ለብዙዎች የዕለት እንጀራ እንደሆነ ሁሉም ይስማሙበታል፡፡ ይሁንና መንግሥት በኩባንያዎቹ አማካይነት ወደ ውጪ በሚላኩ ምርቶች የሚያገኘውን አገራዊ ጥቅም በኩራት የሚናገረውን ያህል ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለሚያበረክቱት ሠራተኞች በበቂ መንገድ ዕውቅና የሰጠ አይመስልም። ዕለታዊ እና ሳምንታዊ የሥራ

ሰዓት መጠንን በተመለከተ ፣የኢትዮጵያ የሠራተኞች አዋጅ፣ አንድ ሠራተኛ በቀን ውስጥ 8 ሰዓት፣ በሳምንት ውስጥ ከ48 ሰዓታት ያልበለጠ ጊዜ ሥራ ላይ እንዲያሳልፍ እና አስቸኳይ ሥራዎች ካሉም አሠሪዎች ሠራተኞቻቸውን ለሥራ መጥራት እንደሚችሉ የሚደነግገው አዋጅ አንዳንድ ኩባንያዎች ማኅበራዊ ሕይወታቸውን በማያማክል ሁኔታ እየተጠቀሙበትእንደሆነ ይታያል። የኩባንያዎቹ ማኅበራት እንዳይመሠረቱ መፈለግ እንዲሁም የመንግሥት በጉዳዩ የነበረው ቸልተኝነት አንዳንዴም እንቅፋት ሆኖ መቀመጥ ሥራውን ከባድ አድርጎታል።

የሠራተኞችንና አሠሪዎች የሥራ ግንኙነት ሕግጋት ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ የተቀመጡትን ሕጎች መብቶችና ግዴታዎች እንዲተገበሩ ማድረግ በሁለቱ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በግማሽ ይፈታል፡ በአጠቃላይም በግል ሴክተሩ የዝቅተኛ ወለል አዋጅ ለመተግበር ቢዘገይም

ውሳኔዎች በተቻለ ፍጥነት እያሳለፉ መሻገር አስፈላጊነቱ ታይቷል።

6. ማጠቃለያ

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያን ጨምሮ በልማት ላይ ያሉ ሃገራት ላይ ያለው የፖሊሲ አውጣጥ ሂደት ግልጽነት እና አስታፊነት የጎደለው ነው። በአጠቃላይ ሲታይ በማንኛዉም ሃገር የፖሊሲ አውጣጥ ባህሪ ውስብስብ ከመሆኑም በላይ በአጭር ግዜ የሚመጣ አይደለም። በአንዳንድ ሃገራት ያለው ሁኔታ ደግሞ ከዚህ የባሰ ነው። ጭራሹኑ ዝግና መንግስት ከፖሊሲ ተመራማሪዎች ሃሳብ የመውሰድ ዝንባሌም ይሁን ፍላጎት አናሳ ነው። የዚህም ዋነኛ ምክንያት፣ በአብዛኛው ግዜ የፖሊሲ ጥናት ተቋማት እና በመንግሥት መካከል ተቀራርቦ የመስራት ልምድ ስለሌለ እንደሆነ አንዳንድ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከፖሊሲ ተቋማት የሚወጡ የጥናትና ምርምር ውጤቶች የመረጃ ከፍተትና የሚጠቀሙበት የማሳመኛ መንገድ ጥራት ችግርም እንድ ሌላ ምክንያት ይነሳል። የሪሰርች አፕቴክ ስልት፣ መሬት ላይ ባለው እውነታ የተመሰረተ ጥናት ብቻ ሳይሆን የጥናቱ ውጤቶች በፖሊሲ አውጪዎች እና ፈፃሚዎች እንዲሁም የልማት ተዋናዮች በቀጥታ ተሳታፊ በሆኑበት የጥናት ሂደት የመነጨውን መረጃና ምክረ-ሃሳብ ወይም እውቀት ተጠቅሞ ተግባራዊ የማድረግ እድሉን በማስፋት ረገድ የሚኖረው አስተዋፃኦ ትልቅ እንደሚሆን እሙን ነው።

በዚህም ምክንያት በFSS እና ACRC ትብብር የተካሄደው የሪሰርች አፕቲክ ፕሮጀክት ሥር የተዳሰሱ የፖሊሲ ጉዳዮችና የመፍትሄ ሃሳቦች ዘግይቶም ቢሆን ተግባራዊ የመሆን እድሉ የሰፋ ነው ተብሎ ይታመናል። (የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሚድያና ኮምዩኒኬሽን ከፍተኛ ባለሞያ ሲሆን፣ በዚህ ፅሁፍ የቀረቡት ሃሳቦችየድርጅቱን ላያንፀባርቁ ይችላሉ)